በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

መዝሙር በእንተ ልደቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

ጥራዝ አንድ

44. የዓለም መድኃኒት
የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተልሔም የተቀደስሽ ነሽ
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ በበረት
አዝ፣
የጥበብ ሰዎች በቅን ሀሳባቸው
ወደአንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው/2/
አዝ፣
ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ ለመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን
ከርቤን/2/
አዝ፣
የሚያድለው ጌታ እውቀት ለሕጻናት
የሚመሰገነው በአፈ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ በበረት
አዝ፣
ሥጋ ለብሶ ቢታይ ረቂቅ መለኮት
በአንድ ላይ ዘመሩ ሰውና መላእክት/2/

45. የድንግል ልዕልና
አሁን ተገለጠ የድንግል ልዕልና
ከእርሷ ተወለደ ሰማያዊ መና
አምላክ አማልክት ቀዳማዊ ቃል
በአንቺ ላይ አደረ ማርያም ድንግል
ከሰማይ ወደ ምድር አብ ቢመለክት
ምንምአላገኘም እንደ አንቺ ንጽሕት
መላእክት በሰማይ እጎታችን ይሉሻል
በንጽሕ በድንጋሌ እነርሱን መስለሻል
46. በኮከብ መፅኡ
በኮከብ መፅው መፅው ሰብአ ሰገል/2/
ለአማኑኤል/4/ ይስግዱ ለአማኑኤል/2/
ትርጉም፡-የጥበብ ሰዎች በኮከብ
እየተመሩ መጡ ለአማኑኤል ይሰግዱ
ዘንድ
47. ጸጽር ቅጠሉ ሠርዶው
ጸጽር ቅጠሉ ሠርዶው ሠንበሌጥ ቄጠ
ማው
በዚያች ወር በዚያች ቀን ለምለም
የነበረው
በእልልታ ዘመሩ በደስታ ተውጠው
ጌታ መወለዱን የምሥራች ሰምተው
እልል በይ ቤተልሔም ሃሌ ሃሌ ሉያ
የፍቅር የሰላም ነሽና ገበያ/2/
የታደሉ እረኞች ያደሩ በትጋት
ብርሃን ሆነላቸው በዕኩለ ሌሊት
ጥሪ ተደርጎለት ከሰማይ ሠራዊት
ለመመልከት በቃ የጌታውን ልደት
አዝ፣
እረኝነት ትንሽ የወራዳ ግብር
ብሎ ሰው በልማድ ደንግጎ ነበር
አምላክ የመረጠው መሆኑን እረኛ
ክርስቶስ ሲወለድ ተረዳነው እኛ
አዝ፣
የተነበዩለት ነቢያት በሙሉ
ጌታ ተወለደ የምሥራች በሉ
ሰውን በመውደዱ ሰማያዊው ንጉሥ
ይኸው ተወለደ እኛን ለመቀደስ
አዝ፣
የሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ሰብአ ሰገል
ሰምተው
ሊሰግዱለት መጡ በኮከብ ተመርተው
ዕጣንና ከርቤ ወርቁንም አመጡ
እንደየሥርዓቱ እጅ መንሻን ሰጡ
አዝ፣
ስለተወለደ መድኅን የኛ ተስፋ
በደል ተወገደ ኃጢአትም ጠፋ
አዝ፣

48. ስብሐት ለእግዚአብሔር
ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት/2/
ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ ሃሌ
ሉያ
ሃሌ ሉያ /3/ ሃሌ ሃሌ ሉያ
ትርጉም፡- ለእግዚአብሔር በሰማያት
ምስጋና ይገባዋል በምድር እርቅ
ተጀመረ
ለሰው ግዕዛኑ/ነፃነቱ/ ሊሰጠው

49. እንዲሆንን ቤዛ
እምሰማያት ወረደ ወእም ማርያም
ተወልደ ተወልደ/2/
ከመይኩን ቤዛ/2/ለኵሉ ዓለም ወለብሰ
ሥጋ ማርያም/2/
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም
ተወለደ/2/
እንዲሆነን ቤዛ/2/ለዓለሙ ሁሉ ለበሰ
የማርያምን ሥጋ/2/

50. በጉል ሰከበ
በጉል ሰከበ በአዕርቅት ተጠብለለ/2/
ቤዛ ኩሉ ዓለም/2/ ዮም ተወልደ/4/
በበረት ተኛ በጨርቅም ተጠቀለለ/2/
የዓለም መድኃኒት/2/ ዛሬ ተወለደ/4/

51. የጥበብ ሰዎች መጡ
ሰማይና ምድር የማይወስኑት
ተወስኖ አየነው በጠባብ ደረት
ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ
አገኘነው ዛሬ በበረት ተኝቶ
የጥበብ ሰዎች መጡ/2/ሰምተውት በዜና
እያበራላቸው ኮከብ እንደ ፋና/2/
ድንግል እመቤቴ ሰላምታ ይድረስሽ
ለአምላክ ወገኖች መመኪያቸው የሆንሽ
µንቺ ተወለደ የዓለም መድኅን
ኩነኔን አጥፍቶ ጽድቅን ሊያወርስን
አዝ...
ጌታችን ሲወለድ በቤተልሔም
ሐዘን ተደምስሶ ሰፈነ ሰላም
እንጨቶች አፈሩ ፍሬ በረከት
ወንዞች ሁሉ ሆኑ ማርና ወተት
አዝ...
ሰብአ ሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእሥራኤል ንጉሥ ወዴት አለ እያሉ
እጅ መንሻውን ሰጡት እንደየሥርዓቱ
ዕጣኑን ለክህነት ወርቁን ለመንግሥቱ
ከርቤውን ለሞቱ
አዝ...

52. ይኸው ተወለደ
ይኸው ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/
እሰይ ተወለደ የዓለም መድኃኒት/3/
ትንቢት ተናገሩ ነቢያቱ በሙሉ
አምላክ ቀዳማዊ ይወርዳል እያሉ
አዝ፣
ሰብአሰገል መጡ ሊሰግዱ በሙሉ
የእስራኤል ንጉሥ ተዋልዷል እያሉ
አዝ፣
ሰብአሰገል መጡ እጅ መንሻ ይዘው
ወርቅ እጣን ከርቤውን ገበሩለት
ሰግደው
አዝ፣
ሕፃናት እንሂድ ከልደቱ ቤት
ውኃ ሆኗልና ማርና ወተት
አዝ፣

53. ለዘተወልደ እምቅድስት

ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል
ምንተንብሎ
ናስተማስሎ ለመድኃኒነ
አርዌ ገዳምኑ አንበሳ ወሚመ/2/
ከራድዮን
ትርጉም፣ከእመቤታችን የተወለደውን
ምን ብለን እንጠራዋለን።
መድኃኒታችን ኢየሱስ
ክርስቶስን በምን እንመስለዋለን በዱር
አንበሳ ነው ወይስ ከራድዮን በሚባል
ወፍ ነው።

ጥራዝ ሁለት

74. ሰማይና መሬት

/መሪቴታ ዮሐንስ/
ሰማይና መሬት የማይወስኑት/2/
ሥጋን ተዋሕዶ ኖየ በልደት /2/
መለኰት ከትስብእት ይለያል ለሚሉ/2/
ቃል ሥጋ ሆነ ሲል ያስረዳል ወንጌሉ
/2/
ቀድሞ በነቢያት ሁሉን ያናገረ/2/
ከሰማያት ወርዶ በድንግል አደረ/2/
ሰማይና ምድር የማይወሰኑት
ሥጋን ተዋሕዶ ታየ በልደት/2/
በቴታችን ልደት ሞት ከጠፋልን/2/
በኖልልኖ እንግለፀው መደሰታችንን/2/
ቴታችን ሲወለድ ለዓለሙ ሁሉ/2/
□ንኳን የሰው ልጆች እንስሳት ዘለሉ/2/
በኰከብ ተመርተው ሰብአሰገል ሄዱ /2/
□ጣንና ከርቤ ወርቅ ይዘው ሰገዱ/2/
ሰማይና መሬት የማይወስኑት/2/
ስ□ን ተዋሕዶ ኖየ በልደት /2/

75. አምላክ ሰው ለመሆን

/መ. ብርሃኑ ውድነህ - ቁ.3/
አምላክ ሰው ለመሆን ስለአፈቀረ/2/
በነቢያት አድሮ /2/ ትንቢት አናገረ
በአዋጅ ተነግሮ ትንቢቱ ሲፈፀም /2/
አምላክ ተወለደ /2/ ከድንግል ማርያም
ከድንግል ማርያም በለበሰው ሥጋ /2/
ኖኖን ወገኖቹን /2/ አለበሰን ጸጋ
ነቢያት በትንቢት ጻድቃን በውዳሴ /2/
ይነጋገራሉ /2/ ከድንግለ ሙሴ
ንጽህናዋን አይቶ ነውር እንደሌለባት /2/
መልአኩ ገብርኤል /2/ ትፀንሻለሽ አላት
ድንግለ ሙሴ (የሙሴ ድንግል)
□መቤታችን ናት።

76. ገብርኤል አወፈየኒ

ገብርኤል አወፈየኒ ህግነ ማርያም
ድንግል/2/
ወበቤተልሔም/2/ ተወልደ አማኑኤል/2/
ትርጉም፦ ገብርኤል ሆይ የድንግል
ማርያምን ልጅ የአማኑኤልን
በቤተልሔም መወለድ አብሥረኝ።

77. አንፈርዓፀ ሰብአሰገል

አንፈርዓፀ ሰብአ ሰገል/2/
ረኪቦሙ ሕጻነ ዘተወልደ ለነ/2/
ትርጉም፦ የተወለደልንን ሕጻን
/ክርስቶስን/ አግኝተው ሰብአ ሰገል ዘለሉ
/ሰቐ□/።

78. ዘነቢያት ሰበክ

ዘነቢያት ሰበክ/2/
ወአስተርዓየ ገሀደ/2/
ትርጉም፦ ነቢያት የሰበኩት በገሀድ
/በግልጥ/ ኖየ።

79. አንፈርዓፀ

አንፈርዓፀ ሰብአ ሰገል/2/
አም□ሆሙ አምፅኡ መትምመ
ትርጉም፦ ሰብአ ሰገል ዘለሉ ሰገዱ/።
የሚያስደንቅ ኖጅ መንሻንም አመጡ።

80. በኮከብ መጽኡ

በኮከብ መጹኡ ሰብአ ሰገል/2/
ኧኸ ይስግዱ ለአማኑኤል/2/
ትርጉም፦ ሰብአሰገል ኮከብ አየመራቸው
ለአማኑኤል ሊሰግዱ መጡ።

81. መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ

/ተምሮ ማስተማር - ቁ. 1/
መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ /2/
የሀበነ ሰላመ ጋዳ ያበውኡ ቁርባነ /2/
ትርጉም፦ ዓለምን ያድን ዘንድ መጣ።
ሰላምንም ይሰጠን ዘንድ። ኖጅ መንሻን
□ንደ ቁርባን ጸስቡሉ።

82. የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው

/ኪ/ጥበብ ወ/ቂርቆስ - ቁ.5/
የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው
ማደሪያዋስ ወዴት ነው/2/
ቦ□ ቍዳናዋ ከወዴት ተቃኘ
ዝናና ወሬዋ ከወዴት ተገኘ
ፈልጐ የገዛት ማነው በቀይ ወርቅ
ባሕሩን ተሻግሮ ስሟን በማወቅ
ማነው ያወረዳት ከደመና በላይ
ድምጿንስ የሰማ ከላይ ከሰማይ
□ርሷን የሚጠሉ ናቸውና ከንቱ
አይቀርላቸውም ኋላ የሞትሞቱ
ሁሉን የሚያውቅ ኖርሱ ኖርሱ
ያውቅላኖል
ቦ□ ቍዳናዋን ጸሳምርላ□ል
በክርስቶስ ፈቃድ በምድር ላይ □የች
□ነሆ ቤት ሠራች ሰባት ዓምድ አቆመች
ጥበብ ግን □ርሱ ነው መትኃኒ□ችን
በሥጋ ተገልጦ ኖኖን ያዳነን
በደሙ ፈውሶ የተወዳጀን
ለ□ርሱ □መረጠን □□በር □መስገን/2/

83. መጽአ ወልድ

ሃሌ ሉያ መጽአ ወልድ ውስተ ዓለም
ሃሌ ሉጸ □ውስተ/2/
ወለብሰ ሥጋነ ሰብአ ኮነ በአርአያ ዚአነ
ትርጉም፦ ከዓለም አስቀድሞ የነበረ
ዛሬም ያለ ዓለምንም አሳልፎ የሚኖር
ወልድ ወደ ዓለም መጣ። ሥጋችንን
ለበሰ። በኖኛ አርአያ ሰው ኾነ።

84. ዘድንግል መናሥግተ

ዘድንግል መናሥግተ ኢያርናኖ/2/
ኢያር□ዘኪሩቤል ኢርክ□ □□ /4/
ትርጉም፦ □እመቤታችንን የድንግልናዋን
ማኅተም አልለወጠም (አልፈታም)
ኪሩቤልም አላየውም አልመረመረውም።

ጥራዝ ሦስት

26. ተወልደ ኢየሱስ

ተወልደ ኢየሱስ በቤተ ልሔም /፪/
ዘይሁዳ በቤተ ልሔም /፪/
አዋልደ ጢሮስ አሜሃ ይሰግዳ /፪/ በቤተ
ልሔም
ትርጉም፡ ኢየሱስ በይሁዳ በቤተልሄም
ተወለደ የጢሮስ ሴት ልጆች ያን ጊዜ
ይሰግዱለታል።

27. ርእይዎ ኖሎት

ዮም ሰማያዊ በኅል ሰከበ ለዘተወልደ
እምቅድስት ድንግል /፪/
ርእይዎ ኖሎት /፪/ አእኰትዎ
መላእክት /፪/
ትርጉም፡ ዛሬ ከቅድስት ድንግል
የተወለደውን እረኞች አዩት መላእክት
አመሰገኑት

28. ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን

/ሰ.ት/ቤት.ማ. ቁ.2/
ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን ወይትሐሠያ
አዋልደ ኢትዮጵያ /፪/
እስመ ተወልደ ብሑተ ልደት መድኃኔ
ዓለም በኢየሩሳሌም መድኃኔ ዓለም /፪/
ትርጉም፡ የጽዮን ተራራሮች ይደሰታሉ፤
የኢትዮጵያም ልጆች ሐጻጽትን
ያደርጋሉ፤
በልደቱ ብቸኛ የሆነ መድኃኔ ዓለም
በኢየሩሳሌም ተወልዷልና።

29. ቤዛ ኩሉ ዓለም

ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ
ቤዛ ኩሉ ዓለም ዮም ተወልደ
የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ
የዓለም ሁሉ መድኃኒት ዛሬ ተወለደ

30. ዮም ተወልደ

ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም
ዮም ተወልደ ከጻድቁ ብርሃን
ትርጉም፦ የዓለም መድኃኒት ዛሬ
ተወለደ
ብርሃንን የሚገልጥ /የብርሃን ጌታ/ዛሬ
ተወለደ

31. በከመ ሰማዕነ (ማኅ/ቅ/ቁ 6)

በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ
በሀገረ እግዚአ ኃያላን በሀገረ አምላክነ
አዳምን ሊያደነው ቃል እንደገባለት
በመስቀል ተሰቅሎ ቤዛ ሊሆንለት
እንደተናገረ ከሰማይ ወረደ
በሰው አμል ታየ በኅል ተወለደ
ነቢያቱ እንዳዩ በትንቢት መነፅር
የያዕቆብን ኮከብ የእሴይን ስር በትር

እኛ ግን በአµል ተገልጦ አየነው
በግዕዘ ህፃናት በጎል አገኘነው
ከህዝቅኤል ምሥራቅ ፀሐይ እንዲወጣ
ወገኑን ሊታደግ መድኅን እንዲመጣ
ነቢያቱ እንዳሉ እኛም እንደሰማን
በአምላµችን ሀገር የሆነውን አየን

ጥራዝ አራት

31. ተቀደሰት ዓለም

ተቀደሰት ዓለም በእንተ ልደቱ /፪/
ተቀደሰት ዓለም/፪/ኢትዮድያ
ተወልደ እምድንግል ሠያሚ
ካህናት ወረደ
ክርስቶስ አክሊለ ሰማዕት/፪/
ትርጉም፡- የካህናት
ሿምያቸው የሰማዕታት
አክሊላቸው ክርስቶስ
ከድንግል ማርያም ተወለደ::
በልደቱም ዓለም/ኢትዮጵያ/
ተቀደሰች፡፡

32. ስብሐት ለእግዚአብሔር
/ቅ/ማርቆስ ሰ/ት/ቤት/

ስብሐት ለእግዚአብሔር
በሰማያት/፪/ /፪/
ወሰላም በምድር/፫/ ሥምረቱ
ለሰብእ
አዝ...
በጎጢአት የወደቀ አዳምን
ሊያነሣ
አምላክ ተወለደ በጎለ እንስሳ
ሕዝቡ ሲኖር ሳለ ጨለማ
ውጦት
አየ ብርሃንን በአምላኩ ልደት
አዝ...
በዳዊት ከተማ በከብቶች
በረት
ይኸው ተወለደ የዓለም
መድኅኒት
ጠፍቶ እንዳይቀርበት ርቆ
ከመንጋ
አምላክ ተወለደ አዳምን
ፍለጋ
አዝ...
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ዕጣን
ከርቤን
ሰው ለሆነው አምላክ አዳምን
ሊያድን
ምነው ባደረገን እኛን እንደ
እረኞች
እንደ ሰብአ ሰገል እንደ ጥበብ ሰዎች /፪/
አዝ...

33. በጐለ እንስሳ

በጐለ እንስሳ /፬/
በጐለ እንስሳ ተወልደ
አማኑኤል/፬/ኧኸ
በእንስሳት በረት/፬/
በእንስሳት በረት ተወለደ
አማኑኤል/፬/ኧኸ

34. አጽነነ ሰማያተ

አጽነነ ሰማያተ ወወረደ
እግዚአብሔር /፪/
እምድንግል ቃል ሥጋ ዚአነ ለብሰ ወነብሩ ትስብእት ወመለኮት /፪/
ትርጉም፡- እግዚአብሔር
በትህትና ራሱን ዝቅ
በማድረግ
ከሰማይ ወረደ ከድንግልም
ሥጋችንን ለበሰ መለኮትና
ሰውም/ሥጋም/ አንድ ሆኑ፡፡

35. አንቺ ቤተልሔም

አንቺ አንቺ ቤተልሔም
የይሁዳ መሬት
ባንቺ ተወለደ የዓለም
መድኃኒት /፪/
የአዳምን ክብር ሲሻ
ቤተልሔም
ለሁሉም ሰላም ቤተልሔም
ጌታ ተወለደ ቤተልሔም
ከድንግል ማርያም
ቤተልሔም
አዝ....
ሕፃኑና እናቱን ቤተልሔም
በበረት አግኝተው ቤተልሔም
የምስራቅ ነገሥታት
ቤተልሔም
እጅ መንሻ አቀረቡ
ቤተልሔም
አዝ....
ቅዱሳን መላእክት ቤተልሔም
አሸበሸቡለት ቤተልሔም
ስብሐት ለእግዚአብሔር
ቤተልሔም
ብለው ዘመሩለት ቤተልሔም
አዝ....

36. ዙፋኑ ነበልባል

/መልአከ ሰላም ታደለ ፊጣ እና አዳነች
አስፋው/

ዙፋኑ ነበልባል መንበሩ
ኪሩቤል
የተመሰገነ ስሙ ነው
አማኑኤል
ከኛ ጋር ሆነ ሰላምን ሰጠን
ስብሐት በአርያም በምድርም
ይሁን

አንቺ ቤተልሔም የኤፍራታ
ምድር
ከፍ ከፍ አረገሽ አምላክሽ
እግዚአብሔር
ተነሽ ተቀበይው እጅሽን
ዘርግተሽ
አማኑኤል ተወልዷል
መድኅን ሆኖልሽ
አዝ...
ዛሬ በኤፍራታ ሕፃኑን አገኘን
ሥጋን ተዋሕዶ መድኃኒት
ሊሆነን
ለዚህ ታላቅ ምሥጢር
ስለተመረጠች
ድንግልም ጠራችው
አማኑኤል አለች
አዝ...
ርቀን የነበርን በደሙ
ቀርበናል
ባርነት ቀርቶልን ልጆች
ተብለናል
ክርስቶስ ተብሎ ክርስቲያን
ላሰኘን
በመላእክት ሥርዓት ቅዱስ
ቅዱስ ቅዱስ እንበል

37. አንፈርአፁ

አንፈርአፁ ሰብአ ሰገል ረኪቦሙ
ሕፃነ /፪/

ዘተወልደ ለነ /፬/ ሕፃን ዘተወልደ
ለነ /፪/

ትርጉም፡- ለእኛ ብሎ
የተወለደውን ሕፃኑን አግኝተው

ሰብአ ሰገል በደስታ ዘለሉ/ሰገዱ/፡፡